# ውድ የሞረሽ ቤተሰቦች፤

ምናልባት ሰምታችሁ ይሆናል፤ የአቶ ደምስ በለጠን ዛሬ (Dec. 22, 2018) ከዚህ ዓለም በሞት የመለየትን ዜና ስናገር ከጥልቅ ሀዘን ጋር ነው። እንደምታውቁት ደምስ የዐማራ ድምጽ ራዲዮ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ከሁለት ዓመት በላይ በዋና አዘጋጅነት ወገናችንን ሲያገለግል ቆይቷል። ወደ አዲስ አበባ የተጓዘውም የዐድራን ሥራ ለመስራትና ለረጅም ጊዜ ያላያቸውን እናቱንና ለሎች በተሰቦቹን ለማየት ነበር። ለመሞቱ ምክንያት የሆነው ነገር ወደፊት የሚጣራ ሲሆን፣ ዝርዝር ሁኔታ ሲገኝ እናሳውቃችኋለን።

ለወንድማችን ደምስ ልጆች፣ ባለቤቱ፣ እናቱና ለሎች ቤተሰቦቹ በዚህ የሐዘን ጊዜ መጽናናትን እንዲሰጥልን ሁላችንም በጸሎታችን እንድናስባቸው ይሁን። ይህ የሁላችንም ሀዘን ስለሆነ ሁላችንም መጽናናትን አግዚአብሄር ያድርግልን።
እንደ ሞረሽ ቤተሰብነታችን ለወንድማችን የቀብር ስነስርአትና ለቤተሰቡ ማድረግ የሚኖርብን ካለ ወደፊት እናሳውቃችኋለን።

ከአክብሮት ጋር፣

አረጋኸኝ ንጋቱ (ዶ/ር)

የሞወዐድ ሊቀመንበር